**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የቦሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽ/ቤት በ1ኛ መንፈቅ ዓመት የተዘጋጀ የ6ኛ ክፍል የግብረ ገብ ትምህርት ሞዴል ፈተና**

**የጥያቄ ብዛት 40**

**የተፈቀደው ሰዓት 1፡00**

**<u>አጠቃላይትዕዛዝ</u>**

ይህ የግብረገብ ፈተና ነዉ:: በዚህ ፈተና ዉስጥ 40 ጥያቄዎች ተካተዋል፤ እያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነዉን አማራጭ የያዘዉን ፊደል በመምረጥ መልስ መስጫ በተሰጠዉ ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይሰጣል:: በፈተና ላይ የተሰጡትን ትዕዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናዉን መስራት ይጠበቅባችኋል:: መልስ የሚሰጠዉ መልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ ነዉ:: በመልስ መስጫዉ ላይ ትክክለኛዉ መልስ የሚጠቆረዉ በእርሳስ ብቻ ነዉ:: ትክክለኛዉን መልስ በማጥቆር ሲሰራ ማጥቆር የተፈቀደዉ ቦታ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደንብ መጥቆር አለበት:: የጠቆረዉን መልስ መቀየር ቢፈለግ በፊት የጠቆረዉን በደንብ በማጥፋት መፅዳት አለበት:: ፈተናዉን ሰርቶ ለመጨረስ የተፈቀደዉ ሰዓት 1 ሰዓት ነዉ:: ፈተናዉን ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠዉ ሰዓት ሲያበቃ ለመስሪያነት የምንጠቀምበትን የመፃፊያ እርሳስ ማስቀመጥና ፈተናዉን መስራት ማቆም አለብን:: ፈተናዉ እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ/ኟ እስከሚነገር ድረስ በቦታችን ተቀምጠን መጠበቅ አለብን:: የሚኮርጅ ወይም በፈተና ሰዓት የፈተናን ህግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናዉ አይያዝለትም፤ ፈተናዉን እዳይፈተን ይደረጋል:: ፈተናዉን መስራት ከመጀመራችሁ በፊት በመልስ መስጫዉ ላይ መሞላት የሚገባዉ መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ መሞላት አለበት::

**ፈተና መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር ክልክል ነው!!**

**መልካም ፈተና!!**

**2018ዓ.ም**



LIVEWORKSHEETS

ትዕዛዝ አንድ ፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልስ ስጡ።

1. ስለ ሀላፊነት ትክክል የሆነው ሀሳብ የቱ ነው?
   - ሀ. ጥሩ ምርጫ አለማድረግ
   - ለ. ለድርጊቶቻችን ተጠያቂነት መውሰድ
   - ሐ. አንድን ነገር በአቅም ልክ አለመስራት
   - መ. ለራስ ባህሪ ተጠያቂ አለመሆን
2. ሀላፊነትን መውሰድ በምን መልኩ ሊጠቅመን ይችላል?
   - ሀ. ራስን ለአደጋ ለማጋለጥ
   - ለ. ተጠያቂነትን ላለመቀበል
   - ሐ. ተጠያቂ መሆን የምንፈልገውን ውጤት ያስገኛል
   - መ. ሀላፊነት የጎደላቸው ውሳኔዎችን ለመወሰን
3. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ከሀላፊነት አይነቶች አይመደብም።
   - ሀ. የግለሰብ ሀላፊነት
   - ለ. የቤተሰብ ሀላፊነት
   - ሐ. ሀገራዊ ሀላፊነት
   - መ. በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ አለመሳተፍ
4. ------- ማለት አንድ ሰው አንድን ነገር እንደሚያደርግ የሚያረጋግጥበት የቃል መግለጫ ነው።
   - ሀ ቃልን መጠበቅ
   - ለ. ሌሎችን መርዳት
   - ሐ. የሀብትአጠቃቀም
   - መ. ሰበብ አለማብዛት
5. በአንድ ሀገር ውስጥ ከገቢ ግብር የሚሰበሰበው ገንዘብ ለምን አገልግሎት ሊውል ይችላል?
   - ሀ. ለመሰረተ ልማት
   - ለ. ለማህበራዊ አገልግሎት
   - ሐ. ለመንግስት አስተዳደራዊ ወጪዎች
   - መ. ሁሉም መልስ ናቸው
6. ከታች ከተዘረዘሩት ውስጥ አካባቢን የመንከባከብ ሀላፊነት ያለበት አካል ማን ነው?
   - ሀ. ግለሰብ
   - ለ. የወረዳ አመራሮች
   - ሐ. ሁሉም የማህበረሰብ አካላት
   - መ. መንግስት
7. ------ማለት ግለሰባዊ እና ማህበራዊ አሰራሮችን ለመምራት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ የማህበራዊ ቡድን መንፈሳዊ እና ቁሳዊ አካላት ስብስብ ነው።
   - ሀ. ጠንክሮ መስራት
   - ለ. ባህል
   - ሐ. ታታሪነት
   - መ. ስራ
8. በጠንካራ የስራባህል ውስጥ ሊካተት የማይችለው ሀሳብ የቱ ነው?
   - ሀ. የሀገር ፍቅር ስሜት እንዲኖረን ያደርጋል
   - ለ. ብዝሀነትን ተቀብለን እንድናሳድግ ይረዳል
   - ሐ. የማህበረሰብ እሴቶችን ለማጠናከር ያግዛል
   - መ. የተረጂነት ስሜትን እንድናዳብር ያደርጋል
9. የታታሪ ሰራተኛ መገለጫ ባህሪያት ውስጥ የማይካተተው ሀሳብ የቱ ነው?
   - ሀ. የስራ ሰዓትን በአግባቡ መጠቀም
   - ለ. የስራ ሰዓትን ለግል ጥቅም ማዋል
   - ሐ. ማህበረሰቡን በሙሉ አቅም ማገልገል
   - መ. ያለውን አቅም ለስራ ማዋል
10. የታታሪ ተማሪ መገለጫ ባህሪያትን የሚገልፀው ሀሳብ የቱ ነው?
    - ሀ. የቤት ስራውን በወቅቱ ሰርቶ መገኘት
    - ለ. በመማር ሂደት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ
    - ሐ. የትምህርት ሰዓትን አክብሮ መገኘት
    - መ. ሁሉም መልስ ናቸው



LIVEWORKSHEETS

11.------ ማለት በአንባቢው እና በሚነበበው ፅሁፍ መካከል የሚካሄድ የተግባቦት ሂደት ነው።

**ሀ.** ንባብ ለ. ማዳመጥ ሐ. መፃፍ መ. መናገር

12. ከሚከተሉት የንባብ ክህሎት ማዳበሪያ ዘዴዎች ውስጥ የፅሁፍን አጠቃላይ ሀሳብ ለማግኘት ሲባል በፍጥነት የማንበብ ሂደትን የሚያሳየው የቱ ነው?

ሀ. የመቃኘት ንባብ **ሐ.** የአሰሳ ንባብ

ለ. አላማ ያለው ንባብ መ. የመረጃ ቃላት

13. ከሚከተሉት የንባብ ክህሎት ማዳበሪያ ዘዴዎች ውስጥ የልዩ ወይም የተወሰነ መረጃ ብቻ ለመፈለግ እና ለማግኘት ሲባል በፍጥነት የማንበብ ሂደትን የሚያሳየው የቱ ነው?

ሀ. የሀረግ ንባብ ሐ. ማስታወሻ መውሰድ

ለ. የዳሰሳ ንባብ **መ.** አላማ ያለው ንባብ

14.------- የመስጠት ችሎታ ያለው ተማሪ ሀላፊነት የሚወስድ እና በራሱ የሚተማመን ይሆናል።

ሀ. ግብረ ገባዊ ውሳኔ **ለ.** ግብረ ገብ ሐ. ችሎታ መ. ቃል መግባት

15. ከግብረ ገባዊ ውሳኔ የመስጠት ችሎታ ባህሪያት ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?

ሀ. አሳቢነት **ሐ.** ምክንያታዊ ውሳኔ

ለ. ምክንያታዊነት መ. መወሰን እና መከታተል

16.--------ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ጥንቃቄ የተሞላበት እና ስልታዊ እርምጃዎችን ይይዛል።

ሀ. አሳቢነት **ሐ.** ችግርን መለየት

ለ. ምክንያታዊ መ. የውሳኔ ውጤት መገምገም

17. ከሚከተሉት የውሳኔ አሰጣጥ ደረጃዎች ውስጥ የመጨረሻ ሊሆን የሚችለውን ምረጡ?

ሀ. ሊከሰቱ የሚችሉ ውጤቶችን መለየት

ለ. የችግሩን መነሻ መለየት

**ሐ.** የውሳኔውን ውጤት መገምገም

መ. ለማነቃቂያ ሊሆኑ የሚችሉ አማራጮችን መፈለግ

18. ውሳኔ የመስጠት ክህሎትን በየትኛው የእድሜ ክልል ላይ ያሉ ዜጎች ቢማሩት ሊጠቅም ይችላል?

ሀ. በልጅነት የእድሜ ክልል **ሐ.** በሁሉም የእድሜ ክልል

ለ. በወጣትነት የእድሜ ክልል መ. በጎልማሳነት የእድሜ ክልል

19. ከሚከተሉት የግብረገባዊ ውሳኔ አሰጣጥ ተግዳሮቶች ውስጥ ሊካተት የማይችለው የቱ ነው?

**ሀ.** ለራስ የሚሰጥ ግምት ሐ. የማረጋገጫ ወገንተኝነት

ለ. የበዛ ቁርጠኝነት መ. ግብረገባዊ ውሳኔ መስጠት

20.----- ማለት አንድ ሰው በጓደኞቹ ዘንድ ለመወደድ እንደ ሌሎቹ የእድሜ እና የማህበራዊ ቡድን ሰዎች ተመሳሳይ ነገሮችን የማድረግ ስሜት ነው።

ሀ. ለራስ የሚሰጥ ግምት ሐ. የግንኙነት ግጭት

ለ. የአቻ ግፊት **መ.** የተገደበ ምክንያታዊነት



LIVEWORKSHEETS

21. እንድ ሰው ስለ ነገሮች ባለው መሰረታዊ ግላዊ እምነት ከእለት ወደ እለት በሚፈፅሙቸው ድርጊቶች መካከል ኢተለዋዋጭ አቋምን የማሳየት ብቃት ምን ይባላል?

ሀ. ምሉዕነት ለ. ወጥነት ሐ. ሀቀኝነት መ. ተጠያቂነት

22. እንድ ሰው ትክክል ነው ብሎ የሚያምንበትን ነገር እንዲተገብር የሚያስችል ውስጣዊ ችሎታ----- ነው፡፡

ሀ. ሀቀኝነት ለ. ድፍረት ሐ. ስለሌሎች ማሰብ ታማኝነት

23. የግብረ ገብ ምሉዕነትን የመላበስ ጠቀሜታ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. በሰዎች ዘንድ እምነትን ማግኘት

ለ. ችግር የመፍታት ችሎታን ወይም ብቃትን ማሳደግ

ሐ. የገቡትን ቃል በቁም ነገር አለመውሰድ

መ. በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነትን ማግኘት

24. እውነተኛ የግብረገብ ምሉዕነትን የተላበሰ ሰው ባህሪን የሚገልፀው ሃሳብ የቱ ነው?

ሀ. ሌሎች ሰዎችን ለማስደሰት ሲል ውሸት ይናገራል፡፡

ለ. ሁኔታዎችን እያየ መቼ ሀቀኛ መሆን እንዳለበት እና እንደሌለበት ይመርጣል

ሐ. በማንኛውም ጊዜ ኢተለዋዋጭ አቋምን ያሳያል፡፡

መ. ከውጭ የሚመጣ ጫናን መቋቋም አይችልም፡፡

25. እንድ ሰው የሚፈፅመው ድርጊት ከሚያሳየው ባህሪ ጋር የማይጣጣም ከሆነ እና እውነተኛ ማንነቱን የማያሳይ ከሆነ ምን ሊባል ይችላል?

ሀ. ሀቀኛ ለ. ታማኝ ሐ. ደፋር መ. ግብዝ /አስመሳይ/

26. በፍቃደኝነት ህግን ላለመጣስ የሚደረግ ማንኛውንም ስምምነት ወይም እንቅስቃሴን የሚገልፀው የቱ ነው?

ሀ. ለህግ ተገዥነት ለ. ህግ ሐ. ሰላምን መጠበቅ መ. በህግ አለመመራት

27. ህግ ከሉላ የሚሰጠው የህይወተ መሰረታዊ ጉዳይ ምን ይባላል?

ሀ. ነፃነት

ለ. ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል

ሐ. የዜጎችን ፍላጎት መጠበቅ

መ. የነፃነት እጦት

28.------- ማለት ከጣልቃገብነት ነፃ ሆኖ ራስን ማስተዳደር ማለት ነው፡፡

ሀ. ሰላምን መጠበቅ

ለ. ሉዓላዊነትን ማስጠበቅ

ሐ. ሙሉነፃነትን ማግኘት

መ. ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል

29. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ለህግተገዥ የሆኑ ዜጎች ባህሪ አይደለም፡፡

ሀ. ህጎች የግል ጥቅምን እንደሚያስጠብቁ ይረዳሉ

ለ. መብቶቻቸውን እና የሀላፊነት ገደባቸውን ያውቃሉ

ሐ. ህግን አለማወቅ ከተጠያቂነት እንደሚያድናቸው ያምናሉ

መ. ሁሉንም ህጎች በአግባቡ በመተግበር ይታወቃሉ

30. ለትምህርት ቤት ህግ ተገዢ ከሆኑ ተማሪዎች ተግባራት ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?

ሀ. የትምህርት ቤት የደንብ ልብስን ለብሶ መገኘት

ለ. የትምህርት ቤት ንብረትን መንከባከብ

ሐ. በፈተና ወቅት መኮረጅ

መ. በክፍል ውስጥ አለመረበሽ



LIVEWORKSHEETS

31. ሰዎች በህይወት የመኖሞብታቸውን ሲያጡ የትኛውን የመብት አይነት አጡ ልንል እንችላለን?

ሀ. ሰብአዊ መብታቸውን ሐ. ሰዓሳዊ መብታቸውን

ለ. ዲሞክራሲያዊ መብታቸውን መ. መልሱ አልተሰጠም

32. ......... ማለት አገልግሎት ሳይሰጡ በተሳሳተ መንገድ ገንዘብ መውሰድ ማለት ነው፡፡

ሀ. ጉቦ መስጠት ለ. ማጭበርበር ሐ. የዘምድና ወገንተኝነት መ. ሙስና

33. ስለ መልካም ባህሪ ትክክል የሆነው ሀሳብ የቱ ነው?

ሀ. በራስ መተማመንን ያዳብራል

ለ. የሰዎች እምነቶች እና አስተሳሰቦች ውጤት ናቸው

ሐ. በሚናገሩት እና በሚፈፅሙት ድርጊቶች መካከል ተመሳሳይነት አለ፡፡

መ. ሁሉም መልስ ናቸው

34. የመልካም ባህሪ መላበስበአት ሊሆን የማይችለው የቱ ነው?

ሀ. ቤተሰብ ለ. ጊዜ ሐ. ምርጫ መ. ገንዘብ

35.---- ማለት ታማኝነትን መተግበር እና ውሸት መናገርን ማስወገድ መቻል ነው፡፡

ሀ. ተለዋዋጭነት ለ. ተጠያቂነት ሐ. ሀቀኝነት መ.ሀላፊነት መውሰድ

36. አላስፈላጊ ስሜትን፣ውስጣዊ ግፊትን እና ምኞትን የመቆጣጠር ብቃት ምን ይባላል?

ሀ. ለህግ ተገዥ መሆን ለ. ራስን መቆጣጠር ሐ. ሌሎችን ማክበር መ. ምሉዕነት

37. የመልካም ስነ ምግባር ባለቤት የመሆን ጠቀሜታ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. በማህበረሰቡ ዘንድ አመኔታ ማግኘት ሐ. የመልካም ግንኙነት መጎደል

ለ. የጓደኛ እጦት መ. ከሌሎች ሰዎች ጋር መጋጨት

38. በኢትዮጵያውያን መካከል ሊተገበር የማይችል የግብረ ገብ እሴት ያልሆነው የቱነው?

ሀ. እንግዳ ተቀባይነት ሐ. የተቸገረ ሰውን መርዳት

ለ. ስርአት ያለው አለባበስ መልበስ መ. ታላላቆችን አለማክበር

39. መልካም በህሪ ማሳደግ የማይጠቅመው ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ------- ነው፡፡

ሀ. ራስን መቆጣጠር ሐ. በአጉል አስተሳሰብ መጠመድ

ለ. ለህግ ተገዥ መሆን መ.የማህበረሰቡን እሴቶች ማክበር

40. አንድ ሰው የሚሰርቅ፣የሚዋሽ እና የሚያጭበረብር ከሆነ ምን ችግር ሊገጥመው ይችላል፡፡

ሀ. ከፍተኛ በራስ መተማመን ይኖረዋል ፡፡

ለ. በራስ የመተማመን ብቃቱ አነስተኛ ይሆናል፡፡

ሐ. በሰዎች ዘንድ እምነት ይጣልበታል፡፡

መ. በማህበረሰቡ ዘንድ እምነት ያገኛል፡፡



LIVEWORKSHEETS